በዚህ በራሪ ጽሁፍ ውስጥ የተካተተው መረጃ የቀረበው ከስራ ቅጥራቸው የሚለዩ ግለሰቦች ያሏቸውን የስራ አጥነት መድን ዋስትና (UI) ጥቅማ ጥቅም መብቶችን የተመለከተ ጠቅላላ መመሪያ ለመስጠት ታስቦ ነው።



Virginia Employment Commission

VIRGINIA CAREER WORKS

ጋር በመተባበር


Virginia Employment Commission
P.O. Box 26441
Richmond, Virginia 23251-6441

www.vec.virginia.gov

የደንበኛ ግንኙነት ማዕከል፥ 1-866-832-2363

VRD/TDD Va Relay ፦ 711


የቨርጂንያ የስራ ቅጥር ኮሚሽን የእኩል ዕድል አሰሪ/ፕሮግራም ነው። ተጓዳኝ እርዳታዎችና አገልግሎቶች በጥያቄ ለአካል ጉዳተኞች ይቀርባሉ። ለቋንቋ ተደራሽነት/ድጋፍ እባክዎ በስልክ ቁጥር 804-584-9841 ይደውሉ። 7/2021




Virginia Employment Commission

# ስለ ስራ አጥነት ጥቅማ ጥቅሞች

## በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

# የሚከተሉት የእርስዎን  የስራ አጥነት መድን ዋስትና ጥቅማ ጥቅሞች ብቁነትና መብት በተመለከተ በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች ናቸው:

**ጥያቄ: የስራ አጥነት መድን ዋስትና (UI ) ይገባኛል ጥያቄዬን እንዴት ማስመዝገብ እችላለሁ?**

መልስ: የይገባኛል ጥያቄዎን በኦንላይን በ www.vec.virginia.gov፣ በስልክ ቁጥር 1-866-832-2363 ደውለው ወይም በቅርብዎ ወደሚገኘው የቨርጂንያ የስራ ቅጥር ኮሚሽን (VEC) ቢሮ ሄደው የወረቀት ማመልቻ በመሙላት ማስመዝገብ ይችላሉ። በአሁኑ ወቅት ወደ VEC የደንበኛ ግንኙነት ማዕከል እየመጡ ያሉት ጥሪዎች ብዛታቸው ከፍተኛ በመሆኑ የተነሳ በኦንላይን ማስመዝገብ ጊዜዎና ጉልበትዎን በከፍተኛ ደረጃ ይቆጥብልዎታል።

**ጥያቄ: የUI ጥቅማ ጥቅም መጠኖች የሚሰሉት እንዴት ነው?**

መልስ: የእያንዳንዱ ግለሰብ የሥራ አጥነት ጥቅማ ጥቅም መጠን እና የቆይታ ጊዜ የይገባኛል ጥያቄውን ከማስመዝገቡ በፊት ከነበሩት የመጨረሻዎቹ አምስት ዕሩብ አመቶች መካከል በአራቱ ውስጥ ባገኛቸው የላብ ዋጋ ክፍያዎች መጠን ላይ የተመሰረተ ነው። ለምሳሌ: ከጥቅምት እስከ ታህሳስ 2020 ዓ.ም ላለው ጊዜ የሚመዘገቡ የUI ሳምንታዊ የክፍያ መጠን ጥያቄዎች ከሀምሌ 1, 2019 እስከ ሰኔ 30, 2020 ዓ.ም ድረስ ከሁሉም አሰሪዎች በተገኙ የላብ ዋጋ ክፍያዎች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ይህ የአስራ ሁለት ወራት ጊዜ "መነሻ ጊዜ" ተብሎ ይጠራል።

**ጥያቄ: ብቁ ለመሆን ምን ያክል ክፍያ ማግኘት ይኖርብኛል?**

መልስ: ለጥቅማ ጥቅሞች ብቁ ለመሆን አንድ ግለሰብ በመነሻ ጊዜ ውስጥ ባሉ ሁለት ዕሩብ አመቶች ውስጥ በጠቅላላው ቢያንስ $2,700 ክፍያ ማግኘት ይኖርበታል።

**ጥያቄ: በUI ጥቅማ ጥቅሞች ስር ምን ያክል አገኛለሁ፤ ለምን ያክል ጊዜ?**

መልስ: በአሁኑ ወቅት ፍተኛው የሳምንታዊ ጥቅማ ጥቅም መጠን $378 ሲሆን ዝቅተኛው መጠን $60 ነው። ግለሰቦች ለከፍተኛው ሳምንታዊ ጥቅማ ጥቅም መጠን ብቁ ለመሆን በመነሻ ጊዜ ውስጥ ባሉ በሁለት ዕሩብ ዓመታት ውስጥ ቢያንስ $18,900.01 ገቢ ማግኘት አለባቸው። ጥቅማ ጥቅሞች ከ12 እስከ 26 ሳምንታት ይለያያሉ እንዲሁም በመነሻ ጊዜ ውስጥ እንደሚገኙት የላብ ዋጋ ክፍያዎች ላይ ተመስርተው ይለያያሉ።

**ጥያቄ: ለማስመዝገብ ምን መረጃ ያስፈልጋል?**

መልስ: የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር፣ አድራሻ እና ስልክ ቁጥር፣ በጣም የቅርብ አሰሪዎ ስም፣ አድራሻ እና ስልክ ቁጥር፣ እና ስራዎን የለቀቁበት ምክንያት። የይገባኛል ጥያቄውን የሚያስመዘግቡት በአካል ቀርበው ከሆነ የማህበራዊ ዋስትና ቁጥርዎ ማረጋገጫ ያስፈልግዎታል።

**ጥያቄ: የይገባኛል ማመልከቻዬን ካስመዘገብኩ በኋላ ምን ይሆናል?**

መልስ: ማመልከቻዎን ካስመዘገቡ በኋላ የግል መለያ ቁጥርን (PIN) ጨምሮ መመሪያዎች በመልዕክት ይደርሱዎታል። ሳምንታዊ የይገባኛል በጥያቄዎን በየሳምንቱ ማስመዝገብ አለብዎት። እባክዎ የሚላኩልዎትን ሁሉንም መመሪያዎች ያንብቡ። ሳምንታዊ የጥቅማ ጥቅሞች የይገባኛል ጥያቄዎን በኢንተርኔት በ www.vec.virginia.gov፣ ወይም በአውቶማቲክ የድምጽ ምላሽ ሲስተም በስልክ ቁጥር 1-800-897-5630 በመደወል ማስመዝገብ ይችላሉ።

**ጥያቄ: የUI ጥቅማ ጥቅሞቼን ከመሰብሰቤ በፊት የመጠበቂያ ጊዜ አለ?**

መልስ: የይገባኛል ጥያቄ ከመመዝገቡ በፊት ሊጀምር የማይችል የአንድ ሳምንት የማይከፈልበት የመጠበቂያ ጊዜ አለ። የመጠበቂያ ጊዜው ሁሉንም የብቁነት መስፈርቶች የሚያሟሉበት የይገባኛል ጥያቄዎን ያስመዘገቡበት የመጀመሪያው ሳምንት ነው። ይህ የማይከፈልበት ሳምንት ከፍተኛ የጥቅማ ጥቅም መጠንዎን አይቀንሰውም። የUI የይገባኛል ጥያቄዎች ከተመዘገቡበት ሳምንት እሁድ ጀምሮ ይጀምራሉ።

**ጥያቄ: በአጠቃላይ ሳምንታዊ የብቁነት መስፈርቶችን ለማሟላት ምን ማድረግ አለብኝ?**

መልስ: ጥቅማ ጥቅሞችን በሚጠይቁበት በእያንዳንዱ ሳምንት:

- በየሳምንቱ ለመስራት ዝግጁ መሆን፣ ፍላጎት ያሉዎ መሆንና መስራት መቻል አለብዎ።
- ጥቅማ ጥቅሞችን በሚጠይቁባቸው በእያንዳንዱ ሳምነት ውስጥ የስራ ፍለጋ የሰነድ ማስረጃዎን ማቅረብ አለብዎት።
- በየትኛውም ጥቅማ ጥቅሞችን በሚጠይቁባቸው ሳምንቶች ሁሉንም ያገኟቸውን የላብ ዋጋዎች ሪፖርት ማድረግ አለብዎት።

**ጥያቄ: የአገልግሎት ክፍያ፣ የዓመት እረፍት ክፍያ፣ የህመምና አደጋ ጥቅማ ጥቅሞች፣ ወይም የበአል ክፍያ ካገኘሁስ?**

መልስ: ያገኟቸው የአገልግሎት ክፍያ፣ የዓመት እረፍት፣ የበአል ክፍያ፣ እና የህመምና የአደጋ ጥቅማ ጥቅሞች የጥቅማ ጥቅም መጠን ሚከፈልበት ከየትኛውም ሳምንት ትክክለኛ ገቢዎች ጋር በተመሳሳይ አኳኋን ከሳምንታዊ የጥቅማ ጥቅም መጠን ላይ ሊቀነሱ ይችላሉ። እነዚህ ጥቅማ ጥቅሞች ወይም ክፍያ የይገባኛል ጥያቄዎ ላይ ተጽእኖ የሚፈጥሩ ከሆነ ይገለጽልዎታል።

**ጥያቄ: ከቀድሞ አሰሪዬ ጡረታ የማገኝ ከሆነ የUI ጥቅማ ጥቅሞቼን መውሰድ እችላለሁ?**

መልስ: በመነሻ ጊዜው ውስጥ ይሰሩ ከነበረበት አሰሪዎ የጡረታ ክፍያ ያገኙ የነበር ከሆነ ሳምንታዊ የጡረታ ክፍያ መጠኑ ከሳምንታዊ የUI ክፍያ መጠን ዶላር ላይ ይቀነሳሉ። የጡረታ መጠኑ ከUI የጥቅማ ጥቅም መጠኑ ጋር እኩል ወይም የሚበልጥ ከሆነ ለUI ጥቅማ ጥቅሞች ብቁ አይሆኑም።

**ጥያቄ: ጥቅማ ጥቅሞቼ ግብር ይከፈልባቸዋል?**

መልስ: ጥቅማ ጥቅሞች የፌደራል የገቢ ግብር ይከፈልባቸዋል። በእርስዎ ጥያቄ ከስራ አጥነት ጥቅማ ጥቅሞችዎ ላይ የፌደራል ግብር ቀንሰን ልንይዝ እንችላለን። በአመቱ ውውጥ ስለተከፈሉዎት ጥቅማ ጥቅሞች የሚገልጽ መግለጫ፣ ቅጽ 1099-G ይላክልዎታል። የትኛውንም የአድራሻ ለውጥ ሲያደርጉ ይህን ለእኛ ማሳወቅ የእርስዎ ኃላፊነት ነው። በተጨማሪም ያገኟቸውን የስራ አጥነት ጥቅማ ጥቅሞች በአመታዊ የግብር ተመላሽዎ ውስጥ ማካተት እና የሚከፈለውን ግብር መክፈል አለብዎት። ከመጠን በላይ እንደተከፈሉዎትና ተመልሰው መክፈል አለባቸው ተብለው የሚወሰኑ ጥቅማ ጥቅሞች ሊቀነሱ ይችላሉ። የአገር ውስጥ ገቢ አገልግሎትን ወይም የግብር አማካሪዎን ያነጋግሩ።

**ጥያቄ: VEC ሌላ ስራ እንዳገኝ ሊረዳኝ ይችላል?**

መልስ: ለUI ጥቅማ ጥቅሞች ብቁ ለመሆን በተጨማሪም ለVEC የስራ ቅጥር ድጋፍ በኦንላይን በ www.vec.virginia.gov የUI የመጀመሪያ የይገባኛል ጥያቄዎን ባስመዘገቡ በአምስት (5) ቀናት ውስጥ መመዝገብ አለብዎ። VEC ለስራ ፈላጊዎች የአካባቢና ግዛት አቀፍ የግል ዘርፍ ስራዎችን እንዲሁም የግዛትና የፌደራል የመንግስት የስራ መደቦችን ጨምሮ የተለያዩ የስራ እድሎችን ያቀርባል። በቁጥር ብዙ በተለያየ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ አሰሪዎች አዲስ ሰራተኛ ለመቅጠር እንዲያግዛቸው VECን የሚጠቀሙ ሲሆን አንዳንድ ኩባንያዎች VECን ሁሉንም ቅጥሮቻቸውን እንዲያካሂድላቸው ይመርጡታል።

